NIC
Nejashi Islamic Centre of Canada

NEJASHI
ኢትዮጵያውያን ካናዳውያን ሙስሊሞች ማሕበር በቶሮንቶ
171 McCormack St. Toronto, ON M6N 1X8
Tel: (416) 658-0081, Cell: (647) 271-6128
www:nejashi.ca Email:info@nejashi.ca

# በቶሮንቶ የሚኖሩ የኢትዮጵያዊያን ሙስሊም ኮምዩኒቲዎች

ለኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ዶ/ር አቢይ አህመድ
አዲስ አበባ ፤ ኢትዮጵያ

በቅድሚያ ለእርሶ እና ለመላዉ ቤተሰብዎ ሰላም፤ ጤናና ፍቅርን እንመኛለን

**ጉዳዩ፤** <u>የኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች ጉዳይ በማስመልከት የቀረበ ግልጽ ደብዳቤ</u>

January 19, 2020

ሀገራችን ኢትዮጵያ ምስቅልቅል ዉስጥ ገብታ ትበታተናለች ፤ ህዝቦቿም የከፋ ስቃይና መከራ ዉስጥ ይዋኙ ቃሉ የሚል ስጋት ባንዣበበት ወቅት የተጋረጠባትን ፈተና በመታደግ ረገድ የእርሶ የክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር እና አጋሮችዎ የዋላችሁት ሚና ምን ያህል ትርጉም እንዳለዉ መቼም የማይዘነጋ ብቻ ሳይሆን ዓለምም የመሰከረዉ እዉነታ እንደሆነ ይታመናል።

የኢትዮጵያ ህዝብ በአንድ የአምባገነን ቡድን ስርዓት ዉስጥ ወድቆ የሚደርስበትን መራር ግፍ መቃወም እንኳን በማይቻልበት የፍርሀት ድባብ ዉስጥ በነበረበት ወሳኝ ወቅት በሰለጠነ መንገድ ታግሎ ያታገለ እና ኢትዮጵያን ዛሬ ላይ ለፈነጠቀዉ የነጻነት ብርሀን እንዲሁም ለህዝባዊዉ ለዉጥ እንቅስቃሴ ፈር ቀዳጅ የሆነዉ የኢትዮጵያ ሙስሊም ማህበረሰብ በተለየ መልኩ ያደረገዉ አስተዋጽኦ ብሎም የከፈለዉ መስዋእትነት ሀገር ያወደሰዉ እንደሆነም እንረዳለን።

በዘመናት ሙስሊሙ ማህበረሰብ ላይ የተፈጸሙ በደሎችን ሁሉ አልፈን ሁሌም ትኩረታችን ወደፊት በጋራ በምንገነባት ሀገራችን ላይ በማድረግ ደፋ ቀና ስንል ቆይተናል። ሆኖም አዲሱን የለዉጥ እርከን ያልተዋጠላቸዉ ወይንም አብሮ መጓዝ የተሳናቸዉ ቡድኖች እና ግለሰቦች ቀድሞ ወደነበረዉ የኋላ ቀርነት አስተዳደር ለመመለስ የሚድሁ እና የሀገራችንን ገጽታ ለማጠልሸት ብሎም የህዝብ የወደፊት ተስፋ እንዲደበዝዝ ሌት ተቀን ሲዳክሩ ይታያሉ።

አዲሲቷን ኢትዮጵያ በሚፈለገዉ መልኩ ለመገንባትም ሆነ ለዉጡን እዉን ለማድረግ ከታሰበ በቅድሚያ ግፍ ሲፈጽሙ እንዲሁም ህብረተሰቡ እንዳይረጋጋ በማድረግ ሚና የሚጫወቱ አካላትን መለየትና መንግስትም እየተፈጸሙ ያሉ ስህተቶችን በመለየት ዉስጡን ሊያጸዳ እንደሚገባ እየጠቆምን  የማስተካከያ እርምጃ መወሰድ እንዳለበትም ግድ የሚል ሲሆን እነዚህ አካላትን ግን ይዞ ሀገራዊ ለዉጥ ማምጣት እንደማይቻል ቅርጹን ለዉጦ እየተፈጸመ ያለዉ ግፍ እና በደል በራሱ በቂ ምስክር ሆኖ እናገኘዋለን። በመሆኑም የለዉጥ ጎዳናዉን መጥነዉ የሚመሩ የአመራር አካላት ማፍራትም ይበጃል።

ባለፉት ሁለት ዓመታት በሀገራችን እስላም ጠልነት እንዲፈጠር ሲሰብኩና ሙስሊሙን ማህበረሰብ ሲያጠቁ የነበሩ አካላት በጠነሰሱት ሴራ በሞጣ ከተማ በመስጂዶች ላይ የተፈጸመዉ በእሳት የማቃጠሉ ሂደት የዚሁ እኩይ ተግባር ዉጤት ነዉ። ድርጊቱም መላዉ የኢትዮጵያኖችን አንገት ያስደፋ የአሸባሪነት ተግባር ሲሆን በከፋ መልኩ የሚያስጨንቀዉ ግን በቀጣይ ሀገሪቱ በምታካሄደዉ መጠነ ሰፊ የለዉጥ እንቅስቃሴ ዉስጥ ይህን መሰል የተንኮል ሴራ ዉስጥ የተሳተፉ አካላት በመንግስት ከፍተኛ ዉሳኔ ሰጪነት ደረጃ ላይ መገኘታቸዉ አሳሳቢነቱን ያሳድገዋል።

መላዉ የኢትዮጵያ ህዝብ የግፍ ቀንበር ተጭኖበት ቀና ማለት በተሳነዉ በዚያ ፈታኝ ወቅት የፍርሀትን ድባብ እንደ ጉም አትንኖ የነጻነት ጎህ እንዲቀድ ፈር ቀዳጅ የሆነዉን ሙስሊሙን ማህበረሰብ የከፈለዉን መስዋእትነት ከግምት ማስገባት ሲገባ ንቀት በተሞላበት ሁናቴ ዳግም ግፍን እንዲያስተናግድ ለማቀድ መዘጋጀት ብልሃት የጎደለዉ ከፍተኛ ዋጋ የሚያስከፍል የቀን ቅዠት ነዉም እንላለንና ሊያስቡበት ይገባል።

ሙስሊሙ ህብረተሰብ የሙብት እና የእምነት ነጻነት ጥያቄዉን አዘዉትሮ እያቀረበ የነበረበት ዋነኛዉ ለሀገር እድገትና ብልፅግና እንዲሁም ከሌሎች እምነቶች ጋር ያለዉን መከባበር ከማሰብ እንጂ ሙብቱ በሙስሊሙ እጅ እንጂ ከማንኛዉም አካል ሊጠይቅ እንደማይገባ ጠንቅቆ ያዉቃል፤ በመሆኑም ዓላማዉ ሙብትን ማስከበር እንጂ መጠየቅን አይሆንም።

የበርካታ መስጂድ ይዞታዎች ተደምረዉ የአንድ ቤተክርስቲያን ያክል ስፋት የሌላቸዉን ዉስን መስጂዶችን ለመገንባት ዉጣ ዉረዱና የህይወት መስዋእትነት መክፈላችን አንሶ በነዚያዉ መስጂዶችም ላይ ጥቃት በመሰንዘር ማፍረስ፤ ማቃጠል እና ህጋዊነታቸዉ እንዳይረጋገጥ እንቅፋት መፍጠር በሚካሄድበት ሀገር ስለ ሀይማኖት እኩልነት ማዉራትም ሆነ በፍትህና በፍቅር ስለ አብሮ መኖር መስበኩም አጠራጣሪ እና አሳሳቢ ሆኖ ታይቶናል።

ሀገራዊ ለዉጡን ተከትሎ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ችግሩን በዘላቂነት ይፈቱታል በሚል ሙስሊሙ ማህበረሰብ ሙሉ በሙሉ ተስፋ አድርጎ የነበረ ቢሆንም ከጊዜ ወደ ጊዜ በሙስሊሙ ማህበረሰብ ላይ አይነቱን ቀያይሮ በየጊዜዉ እየተፈጸሙ ያሉት ጥቃቶች ሲታዩ እምነታችንን እየሸረሸረዉ ይገኛል። በሌላ መልኩ ሚዲያዎችና አክቲቪስቶችም በሙስሊሙ ጉዳይ ያላቸዉን ባህሪና አቋምም በግልጽ የተረዳንበት ወቅት ነዉ።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር የሀገር ጉዳይ ከሁሉም በላይ አሳሳቢ እንደሆነ ለእርሶ ማስረዳት ባይጠበቅብንም የተሰሩ ጥፋቶች ሁሉ ታርመዉ በሙስሊሙ እና በመንግስት መካከል ያለዉ ግንኙነት በመተማመን ላይ እንዲገነባ ለማድረግ በቂ ጥረት እንዲደረግ እየጠየቅን

አሁንም የሞጣ መስጊዶች መቃጠልና የሙስሊሙ ንብረት መውደም ፍትሀዊ የሆነ ምላሽ ባላገኘበት ወቅት በታሪካዊት ሐረር ከትማ ሙስሊሙን ሕብረተሰብ ታሪካዊ ቅርሱን ለማፍረስና የመከባበሩንና የአብሮ የመኖር ዘይቤውን ሊያደፈርስ የሚችል የታቀደ እኩይ ስራ ተስርቶዋል። ይህንን ታሳቢ ያደረገ የእርምት እርምጃ እንዱወሰድ እያሳሰብን ለሰላም ብሎ ሙስሊሙ ሕብረተሰብ የሚያደርገው ትዕግስት ውሱን መሆኑን ልናስገነዝብ እንፈልጋለን።

በ አማራ ክልል በመስጊዶች እና በተመረጡ የሙስሊም ንብረቶች ሱቆች ምግብ ቤቶች ሆቴሎች ላይ የማቃጠል ሂደት ይህ ሙስሊሞችን የማፅዳት ሁኔታ ሽብርና ዕምነትን ማጥፋት የሰውን ዘር ከማጥፋት ያልተናነሰ አለም አቀፋዊ ወንጀል ነው ሰለዝህ የሚከተሉ ወሳኝ ነጥቦች በፌድራል መንግስት የበላይ አስፈጻሚነት በፍጥነት ምላሽ እንዲሰጣቸዉ እና በዘላቂነት መቋጫ ሊሆን በሚችል መልኩ መፍትሄ እንዲበጅላቸዉ በአክብሮት እንጠይቃለን።

1. የፌድራል መንግስት ክስተቱን አጣርቶ ትክክለኛዉን መረጃ ለህዝብ ይፋ እንዲያደርግ
2. የክልሉ መንግስት ለተፈጸመዉ ጥፋት እና ለተሰጠዉ መግለጫ ይቅርታ እንዲጠይቅ
3. በሚዲያዎች ለተፈጸመዉ አድሎአዊነት ይቅርታ በመጠየቅ እርምት በመስጠት መረጃዉን እንዲያስተላልፉ
4. ለተቃጠሉ መስጂዶችና ለሙስሊሙ ንብረቶች የክልሉ መንግስት ካሳ መክፈልና መልሶ ማቋቋም
5. ወንጀሉን የፈጸሙና የተባበሩ የአመራር አካላት በፌድራል በኩል ጉዳያቸዉ እንዲታይ በማለት እንጠይቃለን።

አላህ (ሱ.ወ) ሀገራችንና ህዝቦቿን በሰላም ይጠብቅልን !!!

በቶሮንቶ የሚኖሩ የኢትዮጵያዉያን ሙስሊሞች ኮምዩኒቲዎች

1. ኢትዮጵያ ካናዳዉያን ሙሊሞች ማሕበር በቶሮንቶ
2. ኢስላሚክ ኦሮሞ ሴንተር
3. ሰይድ አህመድ ነጋሽ ሰፖርት ግሩፕ በቶሮንቶ
4. የአፋር ኮምዩኒቲ በቶሮንቶ
5. ሶማሌ ሪጅናል ኮምዩኒቲ በቶሮንቶ
6. ሐረሪ ሔሪተጅ ሴንተር በቶሮንቶ

ቶሮንቶ ፤ ካናዳ